የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የቀድሞ የሳይበር ሰራዊት ልማት ኢንስቲትዩት

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ

# ኦዲት ሪፖርት

ኀዳር /2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የቀድሞው የሳይበር ሰራዊት ልማት ኢንስቲትዩት

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ

# ኦዲት ሪፖርት

የቀድሞው የሳይበር ሰራዊት ልማት ኢንስቲትዩት የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና ማስታወሻዎች ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት የቀድሞው የሳይበር ሰራዊት ልማት ኢንስቲትዩት ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለምአቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ ( የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የቀድሞው የሳይበር ሰራዊት ልማት ኢንስቲትዩት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፤ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፤ ደንብና መመሪያ የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

**የበጀት ሂሳብ**

1. ለመደበኛ ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ብር 40,478,000.00 ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ በየሂሳብ መደቦቹ ከ10% በላይ ብር 34,684,921.82 (85%) ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱ

ከላይ ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የመ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሣያሉ፡፡

ከሠላምታ ጋር

------------------------

አንድነት ብዙሰው

የኦዲት ሥራ አስኪያጅ

ቀን ፡ 30/3/12